# ቀኑ ዛሬ፡ ሥአቱም አሁን ነው!!

ከማተቤ፡ መለሰ፡ ተሰማ

አሁንስ በጣም! እጅግ በጣም! በዛ!! ((ሲሞላ ይፈሣል፡ ሲከር ይበጠሣል)) ነው የሚባለው፡ ከሚገባው በላይ፡ ተገፋንም፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን፡ ሐገርን የሚያክል፡ መተኪያ የማይገኝለት፡ ታላቅ ንብረት፡ ተዘርፈን፡ ባለሐገርነትን፡ የሚያክል፡ መተኪያ የማይገኝለት፡ ታላቅ ክብር፡ ተገፍፈን፡ ሰባዊ መብትና፡ ተፈጥሮዊ፡ ነፃ ነታችንን፡ ተነጥቀን፡ ተንቀንና ተዋርደን፡ እርቃናችንን በመቆም፡ የዓለም ሕዝብ፡ እጣት መቀሰሬያ፡ መሣቂያና መሣለቂያ፡ በመሆን፡ እንደቦቆሎ፡ እሸት ተሸፍነን፡ በማረርና፡ እንደጉንዳን፡ ሰራዊት፡ እጅ ለእጅ፡ ተያይዞ ባለማቋረጥ፡ የሚግተለተለውን፡ ሥቃይና መከራ፡ ሥናሥተናግድ፡ ወራትን፡ አመታት እየተኳቸው፡ የማያቋርጠው፡ የጊዜ ጎርፍ፡ እያጋፈለ አልፎ፡ ዘመን በነበር፡ ጢሻ ውሥጥ፡ ሲሰርግ፡ በአርምሞ፡ መመልከቱን፡ ከተያያዝነው፡ እንሆ፡ 18 አመታትን፡ አሥቆጥረናል።

በእውነት፡ ከዚህ በኋላ፡ ምን እስከሚመጣ፡ ይሆን የምንጠብቀው? እስኪ እያንዳንዳችን፡ ባለንበት፡ ቆም ብለን፡ የተወቃብንን፡ የግፍ አዝመራ፡ እናስታውስ፡ ለመሆኑ እነሱ እነማንናቸው? እኛሥ? እንዲህ የሚጫወቱብን፡ በምን ሥለሚበልጡን፡ ነው? በዚች ምድር ላይሥ፡ ስንት አመት ይሆን፡ የምንቆየው? ከሞትሥ በኋላ ተመልሰን፡ እንኖርባት፡ ይሆን? እስኪ ቆም፡ እንበልና፡ ከአሣለፍሁት፡ ዕድሜየ፡ ውሥጥ ሥንቱን ነው፡ ለዚህ ፈራሽ፡ ሥጋ እንክብካቤ፡ ያዋልኩት? ለሀገሬ፣ ለወገኔና ለልጆቸ፡ በልጠቃላይ፡ መሬት ላይ ለሚቀረው፡ ታሪኬስ፡ ምን ሰርቻለሁ? በማለት፡ እራሣችንን፡ እንጠይቅ፡ ከእኔ ጀምሮ፡ ብዙዋቻችን፡ መልሥ የምናተኝ፡ አይመሥለኝም። ሀፍረት ይሰማን፡ ካልሆነ በቀር፡ ይኸም ከሆነ፡ ጥሩነው፡ ባለፈው ከተፅፅትን፡ ለወደፊቱ፡ ተዘጋጀን፡ ማለትነው፡ አሁን እኮ የቀረን፡ ነገር የለም፡ ሁሉንም፡ አሟጥጠናል፡ መብቴ፡ ተገፈፈ፡ ድምጼ ተዘረፈ፡ ብለን ብንሰለፍ፡ በጥይት፡ ተጨፈጨፍን፣ በጅምላ ታሰርን፣ ተደበደብን፣ ቤት ንብረታችን፣ ተዘረፈ፣ ተሰደድን። አሁንም፡ ተሥፋ ሣንቆርጥ፡ ነፃነታችንን፡ በሰላም፡ ለማግኜት፡ የሰላም፡ እጃችንን፡ ብንዘረጋ፡ የሰላም መልከተኛ፡ እርግቧን፡ ወ/ት ብርቱካንን፡ አለም በቃኝ፡ በመከተት፡ ለሰላም፡ የተዘረጋ፡ እጃችንን፡ ቆረጡት። ስለፍቅር፡ ብንዘምር፡ ቴዲን፡ ከርቸሌ፡ በመከተት፡ ልሣናችንን፡ ዘጉት። የግፉ፡ ብዛት ሥንቱ፡ ትቆጥሮ ያልቃል፡ እንደእኔ፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ተግላችንን፡ ምኞት ሣይሆን፡ ውሣኔ፣ ፍላጎት፡ ሣይሆን፡ ግዴታ ለማድረግ፡ ከምር መወሰን፡ አለብን፡ ጠላትን፡ አሥወግዶ፡ በሰላም፡ እየኖሩ፡ መንፈሥን፡ የደሥታ፡ ውሃ ማጥጣትና፡ ጣፋጭ ማዛውን፡ ማሽተት፡ የሚቻለው፡ የሚካረፋውን፡ መራራ አየር፡ ትንፍሶ በማለፍ፡ ከመሆኑም፡ በላይ ችግርንም፡ መሸሽ ብቻ ሣይሆን፡ ተጋፍጦ፡ ማሸንፍም፡ የወቅቱ፡ ጥያቄ ነው።እናም፡ ለእነዚህ፡ ሁሉ፡ በህግ፡ ተከልለው፡ ለሚፈጸሙብን፡ ህገወጥ ድርጊቶች፡ ማብቂያ፡ የሚይሆነው፡ እንቢታ ነው፡ የአንድ፡ ሀገር ህግ የሚከበረው፡ ለሁሉም፡ እኩል ሲያገለግል፡ ብቻነው፡ ያለዚያ፡ ወያኔስ፡ያወጣውን፡ ህግ፡ አያከብርምና፡ ተጠቃሚው፡ ቢያከብረው እንኳን፡ የተጎዳው፡ ይጥሰው ይበጣጥሰዋል፡ እናም፡ ይህንን፡ ዘራፊዎችን፡ የሚያወድሥ፡ ነፍሰገዳዮችን፡ የሚሾም፣ የሚሸልም፡ ንጹሃንን፡ የሚረሽን፡ በውሸት፡ የተቀተረ፡ በክዕደት፡ የታበተ፡ ህገወጥ ህግ፡ ማፈራረሻችን፡ ቀኑ ዛሬ ሥአቱም፡ አሁንነው።

አይበቃም እንዴ!! በዕውነት፡ ሞትን ይሸሽሁሉ፡ አያመልጠውም፡ የተጋፈጠውም፡ ሁሉ፡ አይጋተውምና፡ አሁን ከፍርሁት፡ ማህጸን፡ የሚወለዱ ምክናያቶችን፡ በሙሉ፡ በሽልነታቸው፡ አስጨንግፈን፡ በቀሬ ጊዜያችን፡ የነበረ፡ ክብርና ማንነታችንን፡ ለማስመለሥ፡ ያመንበትን ሰርተን፡ ውጤቱን፡ ለትውልድና፡ ለታአሪክ፡ ትተን የማለፍ፡ ግዴታ ሥለአለብን፡ የህሌና እና የመንፈስ፡ ጉልበቶቻችንን፡ በማሥተባበር፡ የምንነሣብት፡ ቀኑ ዛሬ ስአቱም፡ አሁን ነው። በቃ፡ ለድሎት፡ የማንጨነቅና፡ ሞትን፡ የምንንቅበት፡ ቀኑ ዛሬ ሥአቱም፡ አሁን ነው። አዋ!!!! የእኛ ትውልድ፡ ከመቃብር፡ በላይ የሚቀር፡ መጥፎ፡ ወይንም፡ ጥሩ ታሪክ፡ ጽፎ የሚያልፍበት፡ ሥአቱ ከቀኑ 11:59 ላይ ነው፡ ያለው፡ ይህችን፡ ውድ ደቂቃ፡ ሣንጠቀምባት፡ ካሳለፍናት፡ ቀጣዩ፡ ቀደም ሲል፡ የደም ዕዳ ስለአለበት፡ ዕድሜ ጠግቦ እንዲሞት፡ አትፍቀድለት፡ በሚል፡ እርዕስ፡ ባቀረብሁት፡ ጽሁፌ፡ ላይ ለማብራራት፡ እንደሞከርሁት፡ ብንፈራው፡ የማይቀረው፡ ጨለማ ነው፡ ያ ከመሆኑ በፊት፡ ግን እኛ ልንቀድም፡ ይገባል፡ ጀግና፡ ስንት ጊዜ ይሞታል፡ ቢለው፡ አንድ ጊዜ አለውና፡ እንደግና፡ፈሬስ፡ ሲለው ፡ ፈሬማ፡ የሚሞተው፡ ሺህ፡ ጊዜነው፡ አለው፡ ይባላልና፡ እኛም፡ ቆመን፡ ሥንሞት ከምንኖር፡ አንድ ጊዜ፡ ሞትን በሞት፡ ሽሮ ማለፍ፡ ሃያውነት፡ ሥለሆነ፡ እያንዳንዳችን፡ በሌሎች፡ መሷዕትነት፡ የድል ባለቤት፡ ለመሆን፡ ማሥላታችንን፡ ትተን፡ እራሣችንን፡ ለሞት እናዘጋጅ፡ እሥኪ፡ እግራችንን፡ ለጠጠር፡ ደረታችንን፡ ለጦር ለመሥጠት፡ እንወሥን፡ እሥኪ፡ ከህሌናችንጋር፡ ከምር እንሟገት፡ ደፈርንም፡ ፈራንም፡ ሞት እንደሆነ፡ የማይቀር፡ የተፈጥሮ፡ ዕዳ ነው፡ ልዩነቱ፡ የክብር፡ ሞት ሞቶ፡ በታሪክ ሲዘከሩ፡ መኖርና፡ የውርደት፡ ሞት ሞቶ፡ በማግሥቱ፡ በቤተሰብ፡ ሣይቀር መረሣት ነው።

ትናንት፡ ከትናንት፡ ወዲያ፡ የወያኔን፡ እኩይ ምግባር፡ ቀድመው በመረዳት፡ ነፍጥ አንሥተው፡ ሲፋለሙ የነበሩ፡ ወገኖቻችንን፡ የተለያዩ፡ ሥምና መልክ፡ በመሥጠት፡ ሣንቅላቀላቸው፡ ብቻ አይደለም፡ ከጥቂቶች፡ በቀር፡ ብዙዋቻችን፡ አይዞአችሁ እንኳን፡ ሣንላቸው፡ ቆይተናል። ዛሬ ግን የቁርጥ፡ ቀን ደርሷል፡ እንሆ፡ ለሀገራቸው፡ ቀናይ፡ ለዲሞክራሲያዊ ሥርአት፡ ታማኝ፡ የሆኑና፡ በሕብረ ብሄራዊ፡ አወቃቅር፡ የተደራጁ፡ ብቃቱም፡ ቆራጥነቱም፡ ያላቸው፡ በሁሉም፡ ዘርፍ፡ ሠፊ ልምድን ያካበቱ፡ ኢትዮጵያዊያን፡ የተሰባሰቡበትና፡ ከብሦት፡ ማህፅን፡ ተፍልቅቆ፡ የወጣው፡ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና፡ የዲሞክራሴ፡ ንቅናቄ፡ ሀገርን የማዳን፡ ጥሬ አቅርቦልናል፡ ለዚህ ወቅታዊ፡ ጥሬ ቅጽበታዊ፡ የአወንታ፡ መልስ፡ መሥጠት፡ ይጠበቅብናል፡ ድልም ሆነ፡ የህሌና ነፃነት፡ ያለ ትግል አይገኝምና።

በአኳያው፡ ደግሞ ይህንን፡ የእናት ሀገር የአርበኝነት፡ ጥሬ ለማክሸፍ፡ ወያኔዎችና፡ ተሥፈኞቻቸው፡ አዲስ እሥትራቴጅ፡ ያሉትን ነጠላ፡ ዜማ በማቀንቀን፡ ላይ ናቸው፡ ጅብን ሊወጉ በአህያ፡ ተጠጉ፡ እንደሚባለው፡ ህዝብ በጦርነት፡ እንዳያልቅ፡ ያሰቡ መሥለውና፡

እራሣቸውን፡ የስላማዊ፡ ትግሉ፡ አካል አሥመሥለው፡ በመቅረብ፡ የሁለገብ፡ ትግሉን፡ የሚያኮላሽ፡ በማር የተሸፈነ፡ መርዛቸውን፡ በመርጨት፡ አንዳንድ፡ የዋህ፡ ኢትዮጵያውያንንም፡ እያሣሳቱ፡ ናቸው። ፋሽስቱ መሬያቸው፡ እረ ከዚያም በላይነው፡ አዶልፍ፡ ሂትለርም፡ ሆነ ዶቸ ሞሦለኒ፡ ለሀገራቸው፡ ጥቅም ሲሉ፡ የውጭ ሀገሩን፡ ሰው ነው፡ የገደሉት፡ ኢዲያሚንንና፡ ቦካሣን፡ ጨምሮ፡ በየትኛውም፡ አህጉርና፡ ሀገር የተነሱ፡ አረመኔዎች፡ ሰውን፡ ቢገድሉም፡ እንኳን፡ የታገሉት፡ ለሀገራቸው፡ ታላቅነት፡ ነው፡ የእኛው ፋሽሥትና፡ አረመኔ፡ ግን እየገደሉ፡ ያሉት ሕዝብንም፡ ሀገርንም፡ ሥለሆነ ለጭካኔያቸው፡ መገለጫ፡ ከፋሽስትና ከአረመኔ፡ በላይ፡ ስም ቢኖር ጥሩ ነበር፡ የሆነው፡ ሆኖ መቸና፡ በምን ምክናያት፡ እንደሆነ፡ ባላስታውሰውም፡ አቶ መለስ በአንድ፡ ወቅት፡ ከበጣም፡ መጥፎ ይሻላል፡ መጥፎ፡ ብለው ነበር፡ የአሁኑ፡ የእናት ሀገርጥሪ፡ ማዳከሚያ፡ ተብሎ፡ በጸረሕዝቡ፡ የውያኔ፡ ቡድን፡ የተያዘው፡ አባላቱን፡ የሰላማዊ ትግል፡ ደጋፊ፡ አሥመሥሎ፡ በእየቦታው፡ በማሥገባት፡ ኢትዮጵያውያንን፡ መከፋፈል፡ ነው። ምክናያቱም፡ እሱ፡ ጠፍጥፎ፡ ከሰራቸው፡ ውጭ ያሉ፡ በሰላማዊ፡ መንገድ፡ የሚታገሉትን፡ ባይወዳቸውም፡ እንዲህ፡ እንደ፡ ወ/ ት ብርቱካን፡ በፈለግ፡ ጊዜ፡ ሰብስቦ፡ ማሰር ሥለሚችል፡ ብዙም፡ ሣያሥጨንቀው፡ ዘመቻው፡ ሁለገብ፡ ትግልን፡ ምርጫቸው፡ ባደረጉት፡ ላይ ሆኗል፡ አዝማች፡ ቃሉም፡ ሰላማዊ፡ ትግሉን፡ ማቀንቀን፡ እዚህ፡ ላይ፡ እንዲታወቅልኝ ፡ የምፈልገው፡ የሰላማዊ፡ ትግሉን፡ እያወገዝሁ፡ አለመሆኔን፡ ነው፡ ይልቁንም፡ ሰርጎ ገቦችን፡ እኛም፡ አውቀናል፡ ብለን በራችንን፡ በመዝጋት፡ ለሀገራችንና፡ ለጋራ፡ ነፃነታችን፡ በጋራ፡ የምንቆምበት፡ ቀኑ ዛሬ ስአቱም፡ አሁን፡ መሆኑን፡ ደጋግሜ፡ ለመናገር፡ እንጅ።

ኢትዮጵያ፡ እንደሀገር፡ እንድተቀጥልና፡ የኢትዮጵያ፡ ህዝብም፡ ከተጫነበት፡ የመከራ ቀንበር፡ እንዲገላገል፡ ከልብ፡ የምንናፍቅ፡ ከሆነ ምኞት፡ የሚጭበጠው፡ በሥራ ነውና፡ ያለምንም፡ ማቅማማት፡  እያንዳንዳችን፡ የዜግነት ድርሻችንን፡ የምናበረክትበት፡ ቀን ቢኖር፡ ዛሬ ሥአቱም፡ አሁን፡ ነው፡ በካህዲው፡ ጎራ ከተሰለፉትና፡ በመሀል፡ ከሰፈሩት፡ ጥቂት፡ ሰዎች፡ ውጭ ሁሉም፡ ኢትዮጵያዊ፡ ማለት፡ ይቻላል፡ የወያኔን፡ ሀገር፡ አጥፊነት፡ በተመለከተ፡ 18 አመት፡ሙሉ በእየፊናው፡ ጽፏል፣ በመድርክ፡ ተናግሯል፡ በእየግዳዳ ጎድጓዳው፡ አምቷል፣ በእየ አደባባዩ፡ ጮኺል፡ የተገኜ፡ ውጤት ግን የለም፡ ቀድሞውንም፡ የተከተልነው፡ የተሳሳተ፡ መንገድ፡ ነበር ማለት፡ ይቻላል፡ ምክናያቱም፡ ከመላው፡ ዓለም፡ በጩኸት፡ ብቻ ነፃ የወጣች፡ ሀገር፡ ብትኖር፡ የእሥራኤሏ፡ እያሪኮ፡ ብቻ ነች፡ ከእሷ በፊትም፡ ሆነ፡ በኋላ በጩኸት፡ ነፃ የወጣ ሀገርና፡ ህዝብ፡ የለም፡ በተለይም፡ በእኛ ሀገር፡ ለወደፊትም፡ በጩኸት፡ ለውጥ እናመጣለን፡ ብለን፡ እንዳናሥብ፡ ከምርጫ 97 ጀምሮ የተፈጸሙብን፡ ድርጊቶች፡ አሥተምረውን፡ አልፈዋል፡ ከአሁን፡ ወዲያ፡ አማራጩም፡ አቋራጩም፡ መንገድ፡ እሾህን፡ በእሾህ፡ እንደሚባለው፡ አመጸኛን፡ በአመጽ፡ መቅጣት፡ እንጅ፡፡ ሀገር፡ ሥትጠፋ፡ ወጋናችን፡ በችግር፡ ሲጠበሥ፡ እያየን፡ በሰላም፡ ለውጥ፡ እናመጣለን፡ የሚለውን፡ ሃሳብ፡ ይዘን፡ የዚህን፡ ነፍሰግዳይ፡ቡድን፡ ዕድሜ ከሚገባው፡ በላይ፡ ማራዘም፡ የለብንም፡ ብቻ ሣይሆን፡ ወያኔና፡ ሰላም፡ አንድ፡ ቀን፡ ይገናኙ፡ ይሆናል፡ የሚለውንም፡ ሀሣብ፡ከአእምሮአችን፡ ፍቀን፡ የምናጠፋበት፡ ቀኑ፡ ዛሬ፡ ሥአቱም፡ አሁን ነው፡ ዛሬ ከመጨረሻው፡ መጨረሻ፡ እርከን ላይ ነው፡ ያለነው፡ የሀገሩን፡ ጥፋት፣ የወገኑን፡ እራብ፣ እርዛት፣ ሞት፡ሥደትና፡ ወርደት፡ ማያት፡ የማይፈልግ፡ ሁሉ፡ አለመግባባቶች፡ ቢኖሩ፡ እንኳን፡ ለእናት፡ ሀገሩ፡ ሲል በመተው፡ ፈቱን፡ በጋራ፡ ወደጋራ፡ ጠላቱ፡ በማዞር፡ ሃቅም ያለው፡ በጉልበቱ፡ ሃብት ያለው፡ በጥሬቱ፡ ዕውቀት ያለው፡ በእውቀቱ፡ ሁሉም፡ የሌለው፡ እንደ እየ እምነትና፡ ሃይማኖቱ፡ በጸሎቱ፡ ሊረባረብበት፡ የሚገባው፡ ጊዜ ቢኖር፡ ቀኑዛሬ ሥአቱም፡ አሁን ነው።

በመጨረሻም፡ አጼ፡ ዩሐንስ፡ በጦርነት፡ ጊዜ የከተት፡ ጥሪ ሲያደርጉ፡ ከተናገሩ፡ ጠቅሼ፡ ልሰናበት((ስማኝ የሀገሬ ሰው፡ ኢትዮጵያ፡ እናትህ፣ ኢትዮጵያ፡ ዘውድህ፣ ኢትዮጵያ፡ ሚስትህ፣ ኢትዮጵያ፡ ልጅህ፣ ኢትዮጵያ፡ መቃብርህ ናት፡ ዛሬ ተወርራለች፡ እንግዲህ፡ የእናትን፡ ፍቅር፡ የዘውድን፡ ክብር፡ የሚሥትን፡ እርዳታ፡ የልጅን፡ ደስታና፡ መቀበሪያ፡ ሀገርን፡ ማጣት፡ ምን ያህል፡ ከባድ፡ እንደሆነ፡ እራሥህ ፍረድ)) ነበር ያሉት።

ማተቤ፡ መለሰ፡ ተሰማ

ታህሣሥ ወር 2001 ዓ.ም

ኢሜል፡ matebemelese@yahoo.com